የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የአፋር ክልል ዲንካራ ጋዜጣ

AFAR REGION DINKARA GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

6ኛ ዓመትቁጥር 43 ሠመራ ሰኔ 2000 ዓ.ም	በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት	6th Year No. 43 Semera June,2000

ማውጫ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የግዥ ስርዓትን ለመወሰን የወጣ አዋጅ..... ገጽ 1

አዋጅ ቁጥር 43/2000

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የግዥ ስርዓትን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ኃላፊቱን በሚገባ ለመወጣት ለሚያደርገው እንቅስቃሴ ሀብትን በቁጠባና ውጤታማ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ ማዋል መሠረታዊ ጉዳይ በመሆኑ፣

የእቃዎች እና የአገልግሎቶች ግዥ እንዲሁም የግንባታ ሥራ ከመንግስት ጠቅላላ ሀብት ከፍተኛውን የወጪ ድርሻ የሚይዝ በመሆኑ፣

የመንግስት ግዥ በቁጠባና ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲፈፀም ከማድረግ በተጨማሪ ሂደቱ ፍትሃዊ፣ ግልጽ እና አድልዎ የሌለበት እንዲሆን ማድረግ ተገቢ ስለሆነ፣

የመንግስት ግዥ ለኢኮኖሚ ልማት ተግባሮች መስፋፋት አጋዥ መሳሪያ መሆን ስላለበት፣

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ተሻሽሎ በወጣው የክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 47 ንዑስ 3(ሀ) መሠረት የክልሉ ምክር ቤት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

ምዕራፍ አንድ

ጠቅላላ

አንቀጽ 1 አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የግዥ ሥርዓት ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 43/2000 ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

አንቀጽ 2 ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሠጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

ሀ/ እቃ ማለት በጠጣር፣ ፈሳሽ በረዝ መልክ የሚገኝ ጥሬ እቃ፣ ምርት፣ መሳሪያ፣ ሽቀጥ እና ኤሌትራክ እንዲሁም ከሚገዛው እቃ ጋር ያልበለጠ ዋጋ ያለው የተከላ፣ የትራንስፖርት የጥገናና ሌላ ተመሳሳይ አገልግሎት ነው።

ለ/ አገልግሎት ማለት ከእቃ፣ ከግንባታ ዘርፍ ሥራ እና ከመክር አገልግሎት ውጪ ያለ ማንኛውም ግዥ ነው።

ሐ/ የግንባታ ዘርፍ ማለት ከሕንፃ፣ ከመንገድ ወይም ከመሠረተ ልማት ሥራ ጋር በተያያዘ የሚከናወን አዲስ የግንባታ፣ የመልሶ ግንባታ፣ የማፍረስ፣ የጥገና፣ የማደስ ሥራ እንዲሁም ተጓዳኝ የሆነና ከዋናው ሥራ ያልበለጠ ዋጋ ያለው አገልግሎት ሲሆን፣ የመገንባት፣ በባለቤትነት የመያዝ፣ ሥራውን የማንቀሳቀስ እና የማስተላለፍ ውሎችን ይጨምራል።

መ/ የምክር አገልግሎት ማለት አማካሪዎች ያላቸውን ሙያዊ ክህሎት በመጠቀም የሚሰጡት የጥናት፣ የዲዛይን፣ የተለዩ ኘሮጀክቶችን የማደራጀት፣ ለደንበኞች ምክር የመስጠት፣ ስልጠና የመስጠት እና እውቀትን የማስተላለፍ የአማካሪነት ባህሪ ያለው የአዕምሮ አገልግሎት ነው።

ሠ/ ግዥ ማለት እቃዎችን፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎችን እና አገልግሎቶችን በግዥ፣ በኪራይ ወይም በማናቸውም ሌላ ተመሳሳይ ውል።

ረ/ ግዥ ፈፃሚ አካል ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በጀት የሚተዳደር የመንግስት መ/ቤት፣ የትምህርት ተቋም እና ተመሳሳይ አቋም ያለው አካል ነው።

ሰ/ የመንግስት ገንዘብ ማለት ከአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መነግስት ግምጃ ቤት ወይም የክልሉ መንግስት ከፌዴራል መንግስት ካገኘው ድጕማ ወይም የሀገርና የውጭ አገር እርዳታና ብድር ለግዥ ፈፃሚ አካላት የውስጥ ገቢ ነው።

ሸ/ የመንግስት ግዥ ማለት በግዥ ፈፃሚ አካላት በመንግስት ገንዘብ የሚከናወን ግዥ ነው።

ቀ/ አቅራቢ ማለት ለግዥ ፈፃሚ አካላት እቃ ወይም አገልግሎት ለማቅረብ ወይም የግንባታ ዘርፍ ሥራ ለማከናወን ውል የገባ ሰው ነው።

በ/ እጩ ተወዳዳሪ ማለት በመንግስት ግዥ እንዲሳተፍ የተጋበዘ ወይም ለመካፈል ያመለከተ ሰው ነው።

ተ/ ተጫራች ማለት የመጫረቻ ሃሳብ ያቀረበ ሰው ነው።

ቸ/ የጨረታ ሰነድ ማለት ተጫራቾች የጨረታ መወዳደሪያ ለማዘጋጀት እንዲውሉ በግዥ ፈፃሚ አካላት የሚዘጋጅ ሰነድ ነው።

ኀ/ የግዥ መመሪያ ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በፋይናንስና ኢኮሃሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ የሚወጣ መመሪያ ነው።

ነ/ ሰው ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርሁደት ነው።

ኘ/ ክልል ማለት የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መነግስት ነው።

አ/ መንግስት ማለት የአፋር ብሔራዋ ክልላዊ መነግስት ነው።

ከ/ የቢሮ ኃላፊ እና ቢሮ ማለት እንደቅደም ተከተሉ የፋይናንስና የኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ እና የፋይናንስና ኢክኖሚ ልማት ቢሮ ነው።

ወ/ ምክር ቤት ማለት የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ነው።

አንቀጽ 3 የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በማናቸውም የክልሉ መንግስት ግዥ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

አንቀጽ 4 ዓለም አቀፍ ግዴታዎች

1. ይህ አዋጅ የፌዴራል መንግስት ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑ መንግስታት ወይም ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ባደረገው ወይም በሚያደርገው ስምምነት ወይም ከስምምነቱ ከመነጨ ግዴታ ጋር የማይጣጣም ከሆነ በስምምነቱ የተመለከተው ይፀናል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመከተው ስምምነት ለኢትዮጵያ ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆኑ ተጫራቾች ልዩ አስተያየት የሚፈቅድ በሚሆንበት ጊዜ ግዥ ፈፃሚ አካል ተፈፃሚ የሚሆነው ልዩ አስተያየት በጨረታ ሰነድ ውስጥ በግልጽ እንዲመለከት ማድረግ አለበት።

አንቀጽ 5 የግዥ መመሪያዎች፡-

1. ቢሮው የዚህን አዋጅና ተከትለው የሚወጡትን ደንቦች አላማዎች ከግብ ለማድረስ እና የአዋጁን ድንጋጌዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።
2. ከአንድ በላይ የሆኑ ግዥ ፈፃሚ አካላት አንድ አይነት እቃ ወይም አገልግሎት ለመግዛት፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራ ለማሠራት የሚፈልጉ በሚሆንበት ጊዜ የቢሮው ኃላፊ አንድ ግዥ ፈፃሚ አካል ወይም ለዚሁ ሥራ የተቋቋመ ድርጅት ግዥ በሚፈፅሙት አካላት ስም ግዥውን በቅንጅት እንዲያከናውን ወይም ግዥ ፈፃሚ አካላት የሚፈልጉትን እቃ፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራ እና አገልግሎት ግዢ በተጠቃለለ ሁኔታ ለመፈፀም የሚያስል የውል ማዕቀፍ እንዲፈርም ሊያዝ ይችላል።
3. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 አፈፃፀም የውል ማዕቀፍ ማለት በቢሮው በተፈቀደለት አካል እና በአቅራቢው መካከል የሚፈረም ግዥ ፈፃሚ አካላት አንድ ዓይነት እቃ፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራ ወይም አገልግሎት በውል ማዕቀፍ በተወሰነ ዋጋ ከአቅራቢው ጋር በሚደረግ የአፈፃፀም ውል ለመግዛት የሚያስችላቸው ስምምነት ነው።

አንቀጽ 6 የሕግ ሰነዶችን ሕዝቡን እንዲያውቅ ስለማድረግ

ይህ አዋጅ እና በዚህ አዋጅ መሠረት በቢሮው ኃላፊ የሚወጡ የግዥ መመሪያዎች ሕዝብ እንዲያውቃቸው መደረግ እና ለአጠቃቀም አመቺ በሆነ መንገድ በሥርዓት መያዝ አለባቸው።

አንቀጽ 7 ኃላፊነትና ተጠያቂነት

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት ስለሚያከናውኑት ግዥ እና ስለውሉ አፈፃፀም ጠቅላላ ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን፣ በተለይም፣
    ሀ. በተገቢው የሰው ኃይል የተደራጀ የግዥ የሥራ ክፍል የማቋቋም፣
    ለ. የጨረታ ኮሚቴ የማቋቋም እና አባላቱን የመሰየም፣
    ሐ. የጨረታ ማስታወቂያዎችን የማውጣት፣
    መ. የጨረታ አሸናፊዎችን የማስታወቅ፣
    ሠ. ውሉ ከመፈረሙ በፊት ግዥ ለመፈፀም የሚያስችል በቂ በጀት መኖሩን የማረጋገጥ፣

ረ. የግዥ ውሎችን የመፈረም፣

ሰ. በተጫራቾች የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መርምሮ ውሳኔ የመስጠት፣

ሸ. የአቤቱታዎችን ቅጂ እና የምርመራ ግኝቶችን እና በግኝቶቹ መሠረት የተሰጠውን ውሳኔ የያዘ ሪፖርት ለቢሮው የማቅረብ፣

ቀ. ከአሸናፊው ጋር የተደረገው ውል ፣ አሸናፊ በሆነባቸው ቃሎችና ሁኔታዎች መሠረት መፈፀሙን የማረጋገጥ፣

በ. እንደአስፈላጊነቱ የግዥ ሥርዓትን የሚያስፈጽሙ ሶስተኛ ወገኖችን የመቅጠር፣ ግዴታ አለባቸው፣

ክፍል ሁለት

የቢሮው አላማ ስልጣንና ተግባር

አንቀጽ 8 የቢሮው ዓላማዎች

ግዥን በሚመለከት የቢሮው አላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. ፍትሃዊ፣ በውድድር ላይ የተመሠረተ፣ ግልጽ፣ አድሎዎ የሌለበት፣ ለመንግስት ገንዘብ ተመጣጣኙን ዋጋ ማስገኘት የሚያስችል የግዥ አፈፃፀም መኖሩን ማረጋገጥ፣
2. የክልሉ መንግስት የግዥ አፈፃፀም የሚመራበት ደረጃ ማውጣት፣
3. የግዥ ፈፃሚ አካላት ይህንን አዋጅ ጠብቀው መሥራታቸውን መከታተል፣
4. በክልሉ መንግስት ውስጥ ያለውን የግዥ አፈፃፀም አቅም ማሳደግ፣

አንቀጽ 9 የቢሮው ተግባሮች

ቢሮው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባሮች ያከናውናል።

1. በመንግስት ግዥ ፖሊሲዎች፣ መርሆዎችና አፈፃፀሞች ላይ የክልሉን መንግስት ማማከት፣
2. በክልሉ መነግስት ውስጥ ያለውን የመንግስት ግዥ አፈፃፃም ሥርዓት ተግባሪዊነት መከታተል፣ ለክልሉ መንግስት ሪፖርት ማድረግ እና በሕግና በአፈፃፀም ሥርዓቱ ላይ የማሻሻያ ሀሳቦች ማቅረብ፣
3. አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የግዥ ስልጠና፣ የግዥ አፈጻፀምን ለመምራት የሚያስፈልገው ችሎታ ሊኖረው የሚገባ ደረጃ፣ ተፈላጊ የሆነው ማስረጃ ዓይነት እና የሙያዊ እድገት የሚከተለው ሂደት እንዲወሰን ማድረግ፣
4. በሥራ ላይ እንዲውሉ የተፈቀዱ መደበኛ የግዥ ሰነዶች፣ አሠራሩን የሚመሩ ቅፅዎች እና ሌሎች ለግዥ አፈፃፀም አግባብነት ያላቸው ሰነዶችን ማዘጋጀት፣ ወቅታዊ እንዲሆኑ ማድረግ፣
5. ከተፈቀዱ መደበኛ የግዥ ሰነዶች፣ አሠራሩን ከሚመሩ ቅፆች እና ሌሎች ለግዥ አፈፃፀም አግባብነት ካላቸው ሰነዶች ውጪ ግዥ የሚፈፀመው ቢሮው በጽሁፍ ስምምነቱን ሲሰጥ ብቻ መሆኑን ማረጋገጥ፣
6. በአንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት ከአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ለመመዝገብ የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን መቀበል፣ መመርመር እና መመዝገብ ለተመዘገቡ አቅራቢዎች የምስክር ወረቀት መስጠት፣
7. በመንግስት ግዥ ውል ውስጥ በተመለከቱ ግዴታዎች ላይ ከፍተኛ ቸልተኝነት በሳየታቸው፣ ስለብቃታቸው የተሳሳተ መረጃ በመስጠታቸው ወይም በአንቀጽ 18 የተመከተውን ዓይነት መማለጃ በመስጠታቸው ምክንያት በመንግስት ግዥ እንዲሳተፍ በቢሮው እገዳ የተደረገባቸውን አቅራቢዎች ዝርዝር መያዝ፣

8. ይህ አዋጅ በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ በተወሰነ ጊዜ ልዩነት የግዥ ፈፃሚ አካላትን ሰነዶች እና ግዥውን በማስፈፀም ሂደት የተከተሉትን አካሄድ መመርመር፣
9. በቢሮው ዋጋ ኃላፊ በሚወሰነው በመንግስት ሊፈፀሙ የታቀዱ ግዥዎችን በጨረታ አሸናፊ የሆኑ አቅራቢዎችን፣ እና ሌሎችንም ሕዝብ ሊያውቃቸው የሚገባ መረጃዎችን መያዝ የሚያስችል ሥርዓት ማደራጀት እና መጠበቅ፣
10. የግዥ አፈፃፀም ይህንን አዋጅ ጠቅቆ የተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ፣

ሀ. በጨረታ ዝግጅት ሂደት የግዥ ምርመራ፣

ለ. በጨረታ አሸናፊ የሆነው ተጫራች በውሉ መሠረት ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ የውል ምርመራ፣

ሐ. በውሉ መሠረት ሥራው ከተጠናቀቀ የክንዋኔ ምርመራ ማካሄድ፣

11. ግዥ ፈፃሚ አካላት በጋራ የሚጠቀሙበት አስገዳጅነት ያለው የእቃና አገልግሎት ዝርዝር በሥራ ላይ መዋል፣ ይኸው ዝርዝር ከአሠራር ጋር የተጣጣመ እና ወቅታዊ እንዲሆን ማድረግ፣
12. ለግዥ አሠራር ሥርዓቶች በሙሉ የሚያገለግል የመጀ ክምችት ማቋቋም፣ ማጐልበት፣ መጠበቅና ወቅታዊነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ማድረግ፣
13. የተቋም እና የሰው ኃይል አቅም ለማጐልበት የሚያስችል የአቅም ግንባታ ፖሊሲና እቅድ እንዲኖር ማድረግ፣
14. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5/2/ በተደነገገው መሠረት ከሚመለከታቸው ግዥ ፈፃሚ አካላት ጋር በመስማማት በየዓመቱ እንደገና እየታየ በሚሻሻል ሥርዓት ግዥያቸው በጋራ ሊፈፀም የሚገባ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች፣ እቃዎችና አገልግሎቶች ዝርዝር ማዘጋጀት፣
15. የሙያና ከሙያ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች አግባብነት ካላቸው በመንግስት ግዥ ለመሳተፍ ፍላጐት ካላቸው አካላት ጋር ተቋማዊ ግንኙነት መፍጠር፣ ማዳበር
16. ስለመንግስት ግዥ አፈጻጸም ጥናት ማካሄድ፣
17. የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባሮችን የማከናወን፣
18. ይህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡ መመሪያዎች በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ፣

አንቀጽ **10** የቢሮው ስልጣን

ቢሮው ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ የሚከተለውን ስልጣን ይኖረዋል።

1. ማናቸውም ግዥ ፈፃሚ አካል ወይም አቅራቢ ሕግ ከሚያዘው ውጪ ስለመፈፀሙ፣ ግዥ በትክክል ስላለማከናወኑ፣ የግዥውን አመራር በትክክል ስላለመፈፀሙ ወይም ስለመመሳጠሩ ሪፖርት የቀረበ ወይም የተረጋገጠ እንደሆነ ከግዥው አፈፃፀም ጋር የተያያዙ መረጃዎች፣ ሰነዶች መዝገቦች እና ሪፖርቶች እንዲቀርቡለት የማዘዝ፣
2. ምስክሮችን የመጥራት፣ ምስክሮችና ግዥው የሚመለከታቸው ወገኖች ቃላቸውን በመሀላ እንዲሰጡ የማድረግ፣ የሂሳብ መዝገብ ኘላን ሰነድ እንዲቀርብለት የማድረግ፣
3. በመንግስት ግዥ አፈፃፀም ላይ ምርመራ እንዲካሄድ ማድረግ ወይም መርመራውን ማከናወን፣ የመንግስት ግዥ ውልና የክንዋኔ ኦዲት ማካሄድ፣

4. ግዥ ፈፃሚ አካላት የጨረታው አሸናፊ የመሆን ውሳኔ በተሰጠበት አኳኋን ግዥውን የፈፀሙ መሆኑን ለማረጋገጥ በግዥው ሂደት ላይ ምርመራ ማካሄድ፣
5. በዚህ አዋጅ ምዕራፍ 8 ውስጥ የተዘረጋውን ሥርዓት በመከተል ግዥ ፈፃሚ አካላት፣ አቅራቢዎች እና ማናቸውም ሌላ ሰው ወይም ድርጅት በግዥው እንቅስቃሴ ተሳትፎ በነበረው ማናቸውም ሰው ላይ የሚያቀርቡትን አቤቱታ የመመርመር፣

ምዕራፍ ሶስት

መሠረታዊ የግዥ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 11 የግዥ ሰነዶች

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት ከመንግስት ግዥ ጋር የተያያዙ መዝገቦችን እና ሰነዶችን ግዥው ከተፈፀመበት ቀን አንስቶ ለ 10 ዓመት ያህል ማቆየት አለባቸው። በዚህ ዓይነት የሚያዙት መረጃዎች የሚከተሉትን ይጨምራሉ።

    ሀ. የሚገዙት እቃዎች፣ የግንባታ ሥራዎች ወይም አገልግሎቶች አጭር መግለጫ

    ለ. የጨረታ ማስታወቂያ፣

    ሐ. የጨረታ መወዳደሪያ ሃሳብ ወይም የወጋ ማቅረቢያ ያቀረ አቅራቢዎች ስምና አድራሻ እንዲሁም በጨረታው አሸናፊ የሆኑ ተጫራቾች ስምና አድራሻ፣

    መ. ለጨረታ ግምገማ የተዘጋጀውን መስፈርት እና ተፈፃሚ የተደረገበትን ሁኔታ የጨረታ ግምገማና የውድድርን አፈፃፀም እና ከተወዳዳሪዎች የቀረበውን የመወዳደሪያ ሃሳብ እና የዋጋ ማቅረቢያ የሚያሳይ አጭር መግለጫ፣

    ሠ. በቀረበው አቤቱታ መሠረት ጨረታውን ለማገድ ወይም ለመሠረዝ ውሳኔ የተሰጠበትን አካሄድ የሚያሳይ መረጃ፣

    ረ. ከግልጽ ጨረታ ውጪ ሌሎች የግዥ ሥርዓቶችን መከተል የተመረጠበትን ምክንያት፣

2. የግዥው ሂደት ተጠናቆ ከአሸናፊው ጋር ውል ከተፈረመ በማናቸውም ምክንያት ውሉ ከተቋረጠ በኋላ የግዥውን ዝርዝር አፈፃፀም የሚያሳየው መረጃ በጨረታ እጩ ተሳታፊ የሆኑ ተወዳዳሪዎች ሲጠይቁ እንዲያዩት መደረግ አለበት። ይሁን እንጂ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ካልታዘዘ እና በፍ/ቤቱ በተሰጠው ትዕዛዝ በተመለከተው መሠረት ካልሆነ በስተቀር ግዥ ፈፃሚው አካል የሚከተሉትን መረጃዎች መስጠት የለበትም፣

    ሀ. የመረጃው ይፋ መሆን በሕግ የማይፈቀድ፣ የሕግ አፈፃፀምን የሚያሰናክል፣ የሕዝብን ጥቅም የሚቃረን፣ የተዋዋዮችን ሕጋዊ የንግድ ጥቅም እንሁም ቀና ውድድርን የሚጐዳ ከሆነ፣

    ለ. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1/መ/ በተመለከተው መሠረት በሳጠር የተዘጋጀውን ሰነድ ካልሆነ በስተቀር ተጫራቾች የቀረበውን የመወዳደሪያ ሃሳብ ከመመርመር እና ከመገምገም ተግባር ጋር የተያያዙ መረጃዎችን፣ እና ተጫራቾች ያቀረቡዋቸውን የመወዳደሪያ ሃሳቦች እና የጨረታ ሰነዶች ይዘት የሚገልፁ መረጃዎች፣

አንቀጽ 12 አድልዎ ያለማድረግ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም እጩ ተወዳዳሪ በዜግነት፣ በዘር ወይም ከመወዳደሪያ መስፈርቶች ጋር ባልተያያዙ ሌሎች ምክንያቶች በመንግስት ግዥ ተሳታፊ እንዳይሆን ሊደረግ አይችልም።

አንቀጽ 13 ልዩ አስተያየት

1. በጨረታ ግምገማ ወቅት፡-

   ሀ. በኢትዮጵያ የተመረቱ እቃዎች እስከ 15%፣ /አስራ አምስት ከመቶ/፣

   ለ. በኢትዮጵያ ኩባንያዎች የሚከናወኑ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች እስከ 7.5%፣ /ሰባት ነጥብ አምስት ከመቶ/፣ ልዩ አስተያየት ይደረግላቸዋል።

2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አፈጻጸም ማናቸውም እቃ ከዋጋው ከ 20% /ሃያ በመቶ/ በላይ በኢትዮጵያ ውስጥ የታከለ ከሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደተመረተ ይቆጠራል።

አንቀጽ **14** የግንኙነት ስልት

1. በግዥ ፈፃሚ አካላትና በእጩ ተወዳዳሪዎች መካከል የሚደረጉ ግንኙነቶች በፅሁፍ መደረግ አለባቸው።በፅሁፍ ያልተደረጉ ማናቸውም ግንኙነቶች በማከታተል በፅሁፍ መረጋገጥ አለባቸው።

2. ቢሮው የመረጃ ልውውጡን ትክክለኛነት እና በምስጢር መጠበቁን ማረጋገጥ የሚያስችሉ ሥርዓቶች መዘርጋታቸውን እና በቴክኒክ ረገድ ተፈላጊ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ሲያረጋግጥ ከፅሁፍ በተጨማሪ ወይም በፅሁፍ ምትክ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ግንኙነት /በኢ..ሜል ወይም በፋክስ/ እንዲደረግ ሊፈቀድ ይችላል።

አንቀጽ **15** የእጩ ተወዳዳሪዎች ብቃት

1. በማንኛውም የመንግስት ግዥ ለመሳተፍ እጩ ተወዳዳሪዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን እና ግዥ ፈፃሚ አካላት ከግዥው ልዩ ባህሪይ በመነሳት የሚያወጧቸውን ሌሎች መስፈርቶች ማማላት አለባቸው።

   ሀ. በሚገቡት ውል መሠረት ለመፈፀም የሚያስችል የሙያና የቴክኒክ ብቃት፣ የፋይናንስ አቅም፣ መሳሪያ እና ሌሎች የመገልገያ ሥፍራዎች፣ ግዥው በሚፈፀምበት ተግባር የሥራ አመራር ችሎታ፣ መልካም ዝና እና የሰው ኃይል ያላቸው፣

   ለ. ውል ለመፈፀም የሚያስችል የሕግ ችሎታ ያለው፣

   ሐ. በእዳ ያልተያዘ፣ ያልከሠረ ወይም የሥራ እንቅስቃሴውን ያላቋረጠ፣ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴው ያልታገደ፣ ወይም በእነዚህ ምክንያቶች ተከሶ በክርክር ላይ ያልሆነ፣

   መ. በኢትዮጵያ የግብር ሕጐች በተደነገገው መሠረት የግብርና የታክስ ግዴታውን የተወጣ፣

2. ግዥ ፈፃሚው አካል እጩ ተወዳዳሪዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩት መስፈርቶች የሚያሟሉ መሆኑን ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ የሰነድ መረጃዎችን ወይም ሌሎች መረጃዎችን እንዲያቀርቡ መጠየቅ አለበት።

3. በዚህ አንቀጽ መሠረት እጩ ተወዳዳሪዎች እንዲያሟሉ የሚጠበቁት መስፈርቶች በጨረታ ሰነድ ወይም የተጫራቾችን የመወዳደሪያ ሃሳብ ለመጠየቅ በሚዘጋጁ ሰነዶች ውስጥ መመልከት ያለባቸው ሲሆን፣ በሁሉም ተጫራቾች ላይ በእኩልነት ተፈፃሚ መሆን አለባቸው።

4. ግዥ ፈፃሚው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የሚቀርቡትን ሰነዶች እና የመመዘኛ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ የእጩ ተወዳዳሪዎችን ብቃት መገምገም አለበት።
5. ግዥ ፈፃሚው አካል ብቃት ያላቸው መሆኑን ለማስረዳት ሀሰተኛ መረጃ የያዙ ሰነዶችን ያቀረቡ እጩ ተወዳዳሪዎች ወይም ብቃታቸውን ለማረጋገጥ ያቀረቡት መረጃ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ወይም ያልተሟላ መሆኑ በማናቸውም ጊዜ የተረጋገጠ እጩ ተወዳዳሪዎች ከጨረታ ውጪ እንዲሆኑ ለመወሰን ይችላል።
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ከ /ለ/ እስከ /መ/ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች እጩ ተወዳዳሪዎች የሚያሟሉ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚከናወነውን ተግባር ቀላል ለማድረግ ቢሮው ከእጩ ተወዳዳሪዎች የሚቀርቡ መረጃዎችን በተቀላጠፈ አሠራር በመመርመር የሥዝገብ የምስክር ወረቀት ይሰጣል። ይህ መረጃ በየጊዜው ወቅታዊ መደረግ አለበት። የአቅራቢዎችን ዝርዝር የሚይዝ አጭር መግለጫ ተዘጋጅቶ አቅራቢዎች ወይም ግዥ ፈፃሚ አካላት በሚጠይቁበት ጊዜ ወሰጠት አለበት። ቢሮው የአቅራቢዎችን የአመዘጋገብ ሥርዓት የሚወስን ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፣

አንቀጽ 16 የእቃና አገልግሎት ዝርዝር

1. ስለ ግዥው ምንነት ትክክለኛና የተሟላ መግለጫ እንዲኖር እንዲሁም እጩ ተወዳዳሪዎች ፍትሀዊና ግልጽ በሆነ ሁኔታ መወዳደር የሚችሉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ግዥ ፈፃሚ አካላት የሚገዙዋቸውን እቃዎች፣ የግንባታ ሥራዎች ወይም አገልግሎቶች ባህሪይ የሚያሳይ የቴክኒክ ዝርዝር ወይም መግለጫ ማዘጋጀት አለባቸው።
2. የቴክኒክ መግለጫው ግዥ ፈፃሚው አካል ሊገዛ የሚፈልገውን እቃ ጥራት፣ ጠቀሜታ፣ ጉዳት የሚያደርስ መሆኑን፣ መለኪያውን፣ መለያውን፣ መጠሪያውን፣ አስተሻሸጉን፣ ምልክቱን፣ ወይም የአመራረቱን ሂደትና ዘዴ እና ተፈላጊውን የሚያሟላ መሆኑ የሚረጋገጥበትን ሥርዓት የሚገልጽ መሆን አለበት።
3. በግዥ ፈፃሚ አካላት የሚዘጋጀው የቴክኒክ ዝርዝር አግባብነት እስካለው ድረስ፣
   ሀ. በዲዛይን ወይም ባህሪያትን በመዘርዘር ላይ ሳይሆን በጠቀሜታ ላይ፣
   ለ. አገራዊ ደረጃ የወጣለት ሲሆን ደረጃውን ወይም ዓለም ዓቀፍ ተቀባይነት ያላቸውን ደረጃዎች ወይም የግንባታ ኮዶች፣ መሠረት ያደረገ መሆን አለበት።
4. የግዥ ፈፃሚውን አካል ፍላጐት በትክክል ለመግለጽ አስቸጋሪ ካልሆነ ወይም ሌላ ዘዴ ካልታጣ በስተቀር የቴክኒክ መግለጫ የተለየ የንግድ ምልክት ወይም ስም፣ ፓተንት፣ ዲዛይን ወይም የተወሰነን አምራች ወይም አገልግሎት ሰጪ የሚጠቅስ መሆን የለበትም። አስገዳጅ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ ወይም ተመሳሳዩን የሚል ሐረግ በእቃና አገልግሎት ዝርዝሩ ውስጥ መታከል ይኖርበታል።

አንቀጽ 17 ጨረታን፣ የመወዳደሪያ ሃሳብን እና የዋጋ ማቅረቢያን ውድቅ ስለማድረግ

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት ጨረታን፣ የዕቃና አገልግሎት አቅርቦት የመወዳደሪያ ሃሳብን እና የዋጋ ማቅረቢያን የግዥ ስምምነት ከመደረጉ በፊት በማናቸውም ጊዜ ውድቅ ማድረግ ይችላሉ።ግዥ ፈፃሚ አካላት ከዚህ በላይ በተመለከተው መሠረት ጨረታን፣ የመወዳደሪያ ሃሳብን፣ የዋጋ ማቅረቢያን ሙሉ በሙሉ ውድቅ ያደረጉበትን ምክንያት በተጠየቁ ጊዜ ለእጩ ተወዳዳሪዎች መግለጽ አለባቸው። ይሁን እንጂ የምክንያቶቹን አግባብነት እንዲያስረዱ አይገደዱም።

2. ግዥ ፈፃሚ አካላት ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከተው መሠረት ጨረታን፣ የመወዳደሪያ ሃሳብን፣ የዋጋ ማቅረቢያን ውድቅ በማድረጋቸው ምክንያት ምንም አይነት ተጠያቂነት አይኖርባቸውም።
3. ጨረታ፣ የመወዳደሪያ ሃሳብን የዋጋ ማቅረቢያ ውድቅ መደረጉን የሚገልጽ ማስታወቂያ ወዲያውኑ ለእጩ ተወዳዳሪዎች እንዲደርስ መደረግ አለበት።
4. ጨረታውን ውድቅ የማድረጉ ውሳኔ የተሰጠው ከጨረታው መዝጊያ ቀን በፊት ከሆነ የጨረታው ሰነዶች ሳይከፈቱ ለእጩ ተወዳዳሪዎች መመለስ አለባቸው።

አንቀጽ 18 በእጩ ተወዳዳሪዎች ስለሚሰጥ መደለያ፣

ማንኛውም እጩ ተወዳዳሪ የግዥ ፈፃሚ አካልን ወይም የሌላ የመንግስት መ/ቤት ኃላፊን ወይም ሠራተኛን ተግባር ወይም ውሳኔ ለማዛባት ወይም ከግዥው አፈጻጸም ጋር በተያያዘ መ/ቤቱ ሊከተለው የሚገባውን አሠራር ለማስለወጥ በመደለያ መልክ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ማናቸውንም ዓይነት ስጦታ የሰጠ ወይም ስጦታ ለመስጠት ቃል የገባ ወይም የሥራ እድል ወይም ሌላ ማናቸውንም የገንዘብ ዋጋ ያለውን ነገር ወይም አገልግሎት መስጠቱ የተደረሰበት እንደሆነ ግዥውን የሚፈፅመው አካል የእጩ ተወዳዳሪውን ጨረታ፣ የመወዳደሪያ ሃሳብ ወይም የዋጋ ማቅረቢያ ውድቅ ማድረግ አለበት። በዚህ ዓይነት የአቅራቢው መወዳደሪያ ውድቅ የተደረገ እንደሆነ ለውሳኔው መሠረት የሆነው ምክንያት በግዥው አፈፃፀም ሰነዶች ላይ መመዝገብ ያለበት ሲሆን፣ መወዳደሪያው ውድቅ የተደረገበትን ምክንያት እጩ ተወዳዳሪው ወዲያውኑ እንዲያውቀው መደረግ አለበት።

ምዕራፍ አራት

የግዥ ዘዴዎችን ስለመምረጥ እና መሟላት ያለባቸው መመዘኛዎች

አንቀጽ 19 የግዥ ዘዴዎች፣

1. የግዥ ዘዴዎች፣
   ሀ. ግለጽ ጨረታ፣
   ለ. ውስን ጨረታ፣
   ሐ. ከአንድ አቅራቢ የሚፈፀም ግዥ፣
   መ. በመወዳደሪያ ሐሳብ መጠየቂያ የሚፈፀም ግዥ፣
   ሠ. በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈፀም ግዥ፣
   ረ. በሁለት ደረጃ የሚካሄድ ጨረታ፣
1. በዚህ አዋጅ በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር ግዥ ፈፃሚ አካላት ማናቸውንም ግዥ ፈፃሚ አካላት ማናቸውንም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈፀም አለባቸው።
2. ግዥ ፈጻሚ አካላት ከግልጽ ጨረታ ውጪ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈፀም የሚችሉት ከዚህ በታች ከአንቀጽ 20-24 በተመለከተት ሁኔታዎች ብቻ ይሆናል።
3. በቂ የኢኮኖሚ ምክንያት ያለ መሆኑን ሲረዳ ቢሮው ከአንቀጽ 20-24 ባልተጠቀሱ ሌሎች ምክንያቶች ግዥ ከግልጽ ጨረታ ውጪ በሌሎች ዘዴዎች እንዲፈፀም በልዩ ሁኔታ ሊፈቅድ ይችላል።

4. ግዥ ፈፃሚ አካላት በምክንያት የተደገፈ የግዥ እቅድ ማዘጋጀት አለባቸው። በዚህ አዋጅ ወይም በግዥ መመሪያው የተዘረጉ የግዥ ሥርዓቶችን ለመሸሽ ግዥ ፈፃሚ አካላት በአንድነት ሊፈፀሙ የሚገባቸውን የእቃ፣ የግንባታ ወይም የአገልግሎት ጊዜዎች መከፋፈል የለባቸውም።

አንቀጽ 20 በውስን ጨረታ ለመጠቀም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት በአንቀጽ 38 በተደነገገው መሠረት በውስን ጨረታ ግዥ ለመፈፀም የሚችሉት የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ነው።
   ሀ. እቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራው ወይም አገልግሎቱ በባህርይው በከፍተኛ ደረጃ ውስብስብ ወይም የተለየ በመሆኑ ምክንያት ከተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ የሚገኝ ሲሆን፣ ወይም
   ለ. በርካታ የጨረታ ሰነዶችን ለመመርመር እና ለመገምገም የሚጠይቀው ከፍተኛ ወጪና ጊዜ እቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራው ወይም አገልግሎቱ ከሚያወጣው አነስተኛ ዋጋ ጋር የማይመጣጠን ሆኖ ሲገኝ፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1/ለ/ የሠፈሩት ሁኔታዎች ተሟልተዋል ለማለት የሚቻለው የግዥው ዋጋ ግምት በግዥ መመሪያ ከተመለከተው ጣሪያ ያልበለጠ ሲሆን ነው።

አንቀጽ 21 ከአንድ አቅራቢ ለሚፈፀም ግዥ ማሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት በአንቀጽ 39 በተደነገገው መሠረት ከአንድ አቅራቢ ግዥ የሚፈጽሙት በእጩ ተወዳዳሪዎች መካከል ውድድር እንዳይኖር ወይም በእጩ ተወዳዳሪዎች መካከል ልዩነት ለመፍጠር ታስቦ መሆን የለበትም። ሆኖም ከሚከተሉት ሁኔታዎች አንዱ ሲያጋጥም ግዥ ፈፃሚ አካላት ከአንድ አቅራቢ ግዥ መፈፀም ይችላሉ።

ሀ. እቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራው ወይም አገልግሎቱ የሚገኘው ከአንድ የተለየ እጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል ሆኖ ሲገኝ፣

ለ. በግዥ መመሪያ የሚደረገው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ ለእቃዎች፣ አገልግሎቶች ወይም ለተገጣሚዎች ተጨማሪ መለዋወጫ እቃዎችን ከመጀመሪያው አቅራቢ መግዛት ሲፈለግ፣ ወይም ከሌላ አቅራቢ ግዥው ቢፈፀም የሚገዛው መሳሪያ ወይም አገልግሎት ግዥ ፈፃሚው አካል ከሚጠቀምበት መሳሪያ ወይም አገልግሎት ጋር የማይጣጣም ሆኖ በመገኘቱ ከመጀመሪያ አቅራቢ ተጨማሪ አቅርቦቶችን፣ አገልግሎቶችን ወይም ተገጣሚዎችን መግዛት አስፈላጊ ሲሆን፣

ሐ. በግዥ መመሪያ የሚደረገው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ያልታሰቡ ሁኔታዎች በማጋጠማቸው ምክንያት በመጀመሪያው ውል ውስጥ ያልተካተቱ ተጨማሪ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ማሠራት አስፈላጊ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ እና ለቴክኒክ ወይም ለኢኮኖሚ ምክንያቶች እነዚህን ተጨማሪ የግንባታ ሥራዎች ከመጀመሪያው ውል ነጥሎ ማሠራት የማይቻል ሆኖ ሲገኝ፣

መ. በግዥ መመሪያ የሚደረገው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አሸናፊው በግልጽ ወይም በውስን ጨረታ ዘዴ ከተመረጠ በኋላ በተፈረመ ውል የመጀመሪያው ኘሮጀክት የተከናወነባቸው ዓይነት ተመሳሳይ ሥራዎች በድጋሜ እንዲሠሩ ማድረግ በማስፈለጉ አዲስ የግንባታ ዘርፍ ሥራ ውል መፈፀም አስፈላጊ ሲሆን፣

ሠ. በግዥ መመሪያ የሚደረገው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ፣የመጀመሪያው የምክር አገልግሎት ውል አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ መጠናቀቁ እና ውሉ እንዲራዘም ማድረግ ቁጠባንና ቅልጥፍናን የሚያስገኝ መሆኑ በመረጋገጡ አገልግሎቱን መቀጠል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣

ረ. ለአጭር ጊዜ የሚቆይ እና ለግዥ ፈፃሚው አካል ልዩ ጥቅም በሚያስገኝ ሁኔታ የሚፈፀም የእቃ ግዥ ሲሆን ነው። ይህ ንዑስ አንቀጽ በመደበኛ አቅራቢነት ያልተሠማሩ ድርጅቶች ለሚሸጡዋቸው አቃዎች የሚያገለግል ሲሆን፣ በመደበኛ አቅራቢነት ከተሠማሩ አቅራቢዎች አዘውትረው የሚፈፀሙ ግዥዎችን አይጨምርም።

ሰ. በጣም አስቸኳይ ከመሆኑ የተነሳ ከባድ ችግር የሚፈጥርና በመ/ቤቱ ሥራ አፈፃፀም ላይ ጉዳትን የሚያስከትል በመሆኑ ምክንያት በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የተፈቀደ ግዥ፣

2. ግዥ ፈፃሚ አካላት በግዥ መመሪያው ከሚወሰን የገንዘብ መጠን ያልበለጡ ግዥዎችን ከአንድ አቅራቢ በሚፈፀም የግዥ ዘዴ በመጠቀም መግዛት ይችላሉ።

አንቀጽ 22 በመወዳደሪያ ሃሳብ መጠየቂያ ግዥ ለመፈፀም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች፣

ግዥ ለፈፃሚ አካላት በአንቀጽ 40 በተደነገገው መሠረት በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ግዥ ለመፈፀም የሚችሉት ለምክር አገልግሎት ወይም ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ ውስጥ የምክር አገልግሎት ዋጋ 50% /ሐምሳ በመቶ/ በላይ ለሚሆን ግዥ ነው።

አንቀጽ 23 በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈፀም ግዥ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች፡-

ግዥ ፈፃሚ አካላት በአንቀጽ 41 በተደነገገው መሠረት በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ ለመፈፀም የሚችሉት ግዥው ቢሮው በሚወጣው የግዥ መመሪያ ከሚወሰነው የገንዘብ መጠን ያልበለጠ እና የሚገዙትም ለገበያ የተዘጋጁ እቃዎች ወይም የታወቀ ገበያ ያላቸው የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ወይም አገልግሎት ሲሆኑ ነው።

አንቀጽ 24 በሁለት ደረጃ ጨረታ ግዥ ለመፈፀም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች፣

ግዥ ፈፃሚ አካላት በአንቀጽ 42 በተመለከተው መሠረት በሁለት ደረጃ ጨረታ ግዥን ለመፈፀም የሚችሉት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው፡-

1. ለሚገዙት እቃዎችና አገልግሎቶች በቂ ዝርዝር ማዘጋጀት በመ/ቤቱ ደረጃ የማይችል ሆኖ ሲገኝ ወይም አገልግሎቶችን በሚመለከት ባህሪያቸውን ለይቶ ለማሳየት የማይችል በሚሆንበት ጊዜና የግዥ ፈፃሚው አካል የግዥ ፍላጐቱን በከፍተኛ ደረጃ ለማሟላት የሚያስችል መፍትሄ ለመፈለግ፣

   ሀ. ጨረታን፣ የእቃና የአገልግሎት አቅርቦት መወዳደሪያ ሃሳብን ወይም የዋጋ ማቅረቢያን በሥራ ላይ ማዋል ሲፈለግ፣

   ለ. በሚገዙት እቃዎች፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎችና አገልግሎቶች ባህርይ ወይም ተፈጥሮ ምክንያት ከአቅራቢዎች ወይም ሥራ ተቋራጮች ጋር ድርድር ማድረግ ሲያስፈልግ፣

2. መጠናቸው በገበያ ላይ ሊውሉ የሚችሉ እቃዎችን የሚጨምር ወይም የምርምር እና የልማት ወጪዎችን ለመተካት ካልሆነ በስተቀር ግዥ ፈፃሚው አካል የምርምር፣ የሙከራ፣ የጥናት እና የልማት ሥራዎችን ለማከናወን የሚያስል ውል መፈፀም ሲፈልግ፣

3. ጨረታ አንዲወጣ ተደርጐ ተጫራቾች ያልቀረቡ እንደሆነ ወይም የቀረቡት ተጫራቾች ውድቅ ሲደረጉ እና መ/ቤቱ ሌላ ጨረታ ቢወጣ ውጤት መገኘቱ አጠራጣሪ ነው ብሎ ሲያምን፣

ምዕራፍ አምስት

የግልጽ ጨረታ አፈፃፀም ሂደት

አንቀጽ 25 የጨረታ ማስታወቂያ

1. የጨረታ ማስታወቂያ አገራዊ ሽፋን ባለው ቢያንስ አንድ ጋዜጣ ላይ መውጣት አለበት። ዝርዝር አፈፃፀሙ በግዥ መመሪያው የሚወሰን ይሆናል።
2. ለእጩ ተወዳዳሪዎች ለጨረታ ማቅረቢያ የሚሰጠው ጊዜ በግዥ መመሪያ ከሚወሰነው አነስተኛ የቀን ብዛት ያነሰ መሆን የለበትም።

አንቀጽ 26 የጨረታ ጥሪ

የጨረታ ጥሪ ቢያንስ የሚከተለውትን መያዝ ይኖርበታል።

1. የግዥ ፈፃሚውን አካል ስምና አድራሻ፣
2. እቃው መቅረብ ወይም ሥራው መጠናቀቅ ያለበትን ጊዜ ጨምሮ የእቃውን፣ የግንባታ ሥራውን እና የአገልግሎቱን አጭር መግለጫ፣
3. የጨረታውን ሰነድ ለማግኘት መሟላት ያቀባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች እና የጨረታ ሰነዱ የሚገኝበትን ቦታ፣
4. የጨረታ መወዳደሪያ ሃሳብ የሚቀርብበት ቦታ እና የማቅረቢያው የመጨረሻ ጊዜ፣
5. ጨረታው የሚከፈትበት ቦታ እና ጊዜ እንዲሁም ተጫራቾች ወይም ተወካዮች ጨረታው ሊከፈት መገኘት የሚችሉ መሆኑን የሚገልጽ ማሳሰቢያ፣

አንቀጽ 27 የጨረታ ሰነድ

1. በተጫራቾች መካከል የሚደረገው ውድድር በተሟላ፣ ገለልተኛና ተጨባጭ መሠረት ባለው ሁኔታ እንዲካሄድ ለማድረግ የጨረታው ሰነድ በቂ መረጃ የያዘ መሆን አለበት። በተለይም ሰንዱ የሚከተሉትን ሊያካት ይገባል።

ሀ. የጨረታ ሰነዱን ለማዘጋጀትና ለማቅረብ አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን፣

ለ. የጨረታ ሰነዱን ማስከበሪያ የመጨረሻ ቀን፣ የጨረታ ሰነዱ የሚላክበትን አድራሻ፣ የጨረታው ሰነዱ የሚከፈትበትን ቀን፣ ሰዓት እና ቦታ፣ እንዲሁም የተጫራቾች ወኪሎች በጨረታው መክፈቻ ሥነ-ሥርዓት ላይ ሊገኙ የሚችሉ መሆኑን የሚገልጽ መረጃ፣

ሐ. የጨረታ መወዳደሪያ ሃሳብ ማቅረቢያ ቅፆች፣ እንዲሁም አግባብነት እስካለው ድረስ የጨረታ ማስከበሪያ ቅፆች፣

መ. ከዋናው የጨረታ ሰነድ ጋር መቅረብ ያለባቸውን ተጨማሪ /ኮፒዎች/፣

ሠ. የውሉን አጠቃላይ እና ልዩ ሁኔታዎች፣

ረ. እንደ አግባብነቱ እቃውን እና አገልግሎቱን ለማቅረብ ወይም የግንባታ ዘርፍ ሥራውን ለማጠናቀቅ ይወሰዳል ተብሎ የሚገመተውን የጊዜ ገደብ ጨምሮ ተፈላጊውን የእቃና አገልግሎት ዝርዝር፣

ሰ. ተጫራቹ በጨረታው ለመሳተፍ ብቃት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚቀርባቸውን መረጃዎች ዓይነት እንዲሁም የፋይናንስ አቋሙን እና በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገበ መሆኑን ለማረጋገጥ ማቅረብ ያለበትን መረጃ፣

ሸ. ጨረታው ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ፣

ቀ. ጨረታውን ለመገምገም እና በጨረታው አሸናፊ የሆነውን ለማስታወቅ የሚያገለግሉ መስፈርቶችን እና ለአያንዳንዱ መስፈርት የተሰጠውን ነጥብ፣

በ. ግዥውን የሚፈጽመው አካል የጨረታው አሸናፊ ይፋ ከመደረጉ በፊት በማናቸውም ጊዜ ጨረታውን የመሠረዝ መብት ያለው መሆኑን፣

አንቀጽ 28 የጨረታ ሰነድ ሽያጭ

የጨረታ ሰነዶች ለጨረታው ሰነድ ዝግጅት እና ሰነዱን ለእጩ ተወዳዳሪዎች ለማቅረብ ከወጣው ወጪ ባልበለጠ ዋጋ፣ በተፋጠነ ሁኔታ እና በጨረታ ማስታወቂያ በተገለፀው አኳኋላ ለእጩ ተወዳዳሪዎች እንዲደርሱ መደረግ አለበት።

አንቀጽ 29 በጨረታ ሰነድ ላይ ስለሚደረግ ማሻሻያ

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት በራሳቸው ወይም የጨረታ ሰነድ ከጊዜ እጩ ተወዳዳሪዎች በሚቀርቡ ጥያቄዎች መነሻ የጨረታ ሰነዱ ማቅረቢያ ጊዜ ገደብ ከማለፍ በፊት የጨረታ ሰነዶችን ይዘት ለማሻሻል ይችላሉ።
2. የተደረገው ማሻሻያ በፅሁፍ ተዘጋጅቶ የጨረታ ሰነዶችን ለገዙ እጩ ተወዳዳሪዎች ሁሉ በተገቢው ሁኔታ በእኩል እንዲደረስ መደረግ አለበት።
3. ግዥ ፈፃሚው አካል የጨረታ ሰነዱን የዘት ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ያገኘው እና በማሻሻያው የተመለከቱ ማስተካከያዎችን ለማድረግ በቂ ጊዜ የሌለ መሆኑን የተረዳ እንደሆነ እጩ ተወዳዳሪዎች ማሻሻያውን መሠረት አድርገው የጨረታ ሰነዱን ለማዘጋጀት በቂ ጊዜ እንዲኖራቸው ለማድረግ የግዥውን ባህርይ መሠረት በማድረግ የጨረታውን ማቅረቢያ ጊዜ ለተወሰኑ ቀናት ሊያራዝም ይችላል።

አንቀጽ 30 የጨረታ ማስከበሪያ

1. በዚህ አዋጅ በተለይ ካልተወሰነ በስተቀር ግዥ ፈፃሚ አካላት በሚያዘጋጁት የጨረታ ሰነድ ተጫራቾች ከጨረታ ሰነዶቻቸው ጋር በተቀማጭ ገንዘብ ወይም በጨረታ ዋስትና መልክ የጨረታ ማስከበሪያ የማቅረብ ግዴታ እንዳለባቸው መግለጽ አለባቸው። የጨረታ ማስከበሪያው መጠን በጨረታው ኃላፊነት በተሞላው ሁኔታ የማይሳተፉትን ለማስቀረት የሚያስችል ሆኖ በግዥ መመሪያው ከተወሰነው መጠን ያልበለጠ መሆን አለበት።
2. የጨረታ ማስከበሪያው ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ተጫራቹ ራሱን ከውድድሩ ካገለለ ወይም አሸናፊውን ተጫራች በሚመለከት አሸናፊነቱ ከተገለፀለት በኋላ ውሉን ለመፈረም ፈቃደኛ ሆኖ ካልተገኘ ወይም እንዲያቀርብ የተጠየቀውን የውል ማስከበሪያ ካላቀረበ የጨረታ ማስከበሪያው ውርስ ይደረጋል።

አንቀጽ 31 የጨረታ ሰነድ ስለማቅረብ ስለመቀበል

1. የጨረታ ሰነድ በፅሁፍ ተዘጋጅቶና ተፈርሞበት በታሸገ ኢንቨሎፕ ውስጥ ሆኖ በጨረታ ማስታወቂያው ከተመለከተው የጊዜ ገደብ በፊት በተገለፀው ቦታ ገቢ መደረግ አለበት።
2. የጨረታው ሰነድ ትልቅ በመሆኑ በጨረታ ሳጥን ውስጥ ሊቀመጥ የማይችል ከሆነ ግዥ ፈፃሚው አካል የጨረታ ሰነዱ ገቢ የተደረገበትን ቀንና ሰዓት የሚሳይ ደረሰኝ ለተጫራቹ መስጠት አለበት።
3. ከዚህ በላይ በቁጥር 2 የተገለፀው ዓይነት የጨረታ ሰነድ ለጨረታ ማቅረቢያ ከተወሰነው ጊዜ በኋላ ከቀረበ ላይከፈት ለተጫራቹ መመለስ አለበት።

አንቀጽ 32 ጨረታን ስለመክፈት

1. ግዥ ፈፃሚው አካል በጨረታ ሰነዱ የተመለከተው ለጨረታ ሰነድ ማቅረቢያ የተወሰነው የጊዜ ገደብ እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ፣ የጨረታ ሰነድ ከማቅረቢያ የጊዜ ገደብ በፊት የተረከባቸውን የጨረታ ሰነዶች መክፈት አለበት።
2. ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በጨረታ ሰነድ መክፈቻ ሥነ-ሥርዓት ላይ እንዲገኙ መጋበዝ አለባቸው።
3. የተጫራቾች ስም እና በእያንዳንዱ የጨረታ ሰነድ የቀረበው የመጫረቻ ወጋ ድምር ከፍ ባለ ድምፅ መነበብ እና መመዝገብ እንዲሁም ተጫራቾች በጠየቁ ጊዜ የተመዘገበውን ዝርዝር እንዲያገኙ መደረግ አለበት።

አንቀጽ 33 የጨረታ ሰነዶችን ስለመመርመር እና ስለመገምገም

1. ጨረታውን ለመመርመርና ግምገማውን ለማከናወን የሚረዳ ሆኖ ሲገኝ፣ ግዥ ፈፃሚው አካል ተጫራቾች ባቀረቡት የጨረታ ሰነድ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጡ ሊጠይቅ ይችላል። ሆኖም የዋጋ ለውጥን ጨምሮ በጨረታው ሰነድ ላይ መሠረታዊ ለውጥ የሚያስከትል ሃሳብ ማቅረብ ወይም መፍቀድ አይችልም።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም ግዥ ፈፃሚው አካል በጨረታ መርመራው ወቅት የተገኙ የሂሳብ ስህተቶችን ለማረም ይችላል። ግዥ ፈፃሚው አካል እነዚህን ማስተካከያዎች የጨረታ ሰነድን ላቀረበው ተጫራቾች በአፋጣኝ መግለጽ አለበት።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ግዥ ፈፃሚው አካል ጨረታው የተሟላ ነው ብሎ ሊቀጥል የሚችለው በጨረታው ሰነድ የተመለከቱትን ተፈላጊ ሙሉ በሙሉ የሚያሟላ ሆኖ ሲያገኘው ነው።
4. በጨረታው ሰነድ ከተዘረዘሩት ባህሪያት፣ የውል ቃሎች፣ ሁኔታዎች እና ሌሎች ተፈላጊ ነጥቦች ጋር በተወሰነ ደረጃ ልዩነት ቢኖረውም መሠረታዊ የሆነ ለውጥ እና ልዩነት እስከሌለው ድረስ ወይም የጨረታው ቁምነገር ሳይለወጥ ሊታረም የሚችል ጥቃቅን ስህተት ወይም ግድፈት ቢኖረውም ግዥ ለፈፃሚው አካል ጨረታውን እንደተሟላ አድርጎ ሊቀበል ይችላል።ማናቸውም ልዩነት እስከተቻለ ድረስ በአህዝ ተገልፆ በጨረታ ግምገማ እና ውድድር ወቅት ከግምት ውስጥ መግባት አለበት።
5. ማናቸውም ግዥ ፈፃሚ አካል ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የሚያሟሉ ጨረታዎችን ለውድድር ማቅረብ የለበትም።

   ሀ. ተጫራቾች በአንቀጽ 27/ሰ/ የተጠቀሱትን መስፈርቶች ማሟላት የማይችል ሆኖ ሲገኝ፣

   ለ. ተጫራቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የተደረገውን የሂሳብ ማስተካከያ የማይቀበል ሆኖ ሲገኝ፣

   ሐ. የቀረበው የጨረታ መወዳደሪያ ሃሳብ ተፈላጊውን የማያሟላ ሆኖ ሲገኝ፣
6. ግዥ ፈፃሚው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 በተደነገገው መሠረት አሸናፊውን ተጫራች ለመምረጥ በጨረታ ሰነዱ በተመለከተው ሥርዓት እና የግምገማ መስፈርት ተፈላጊውን ያሟሉ የጨረታ ሰነዶችን መገምገምና ማወዳደር አለበት። በጨረታ ሰነድ ያልተመለከተ የማወዳደሪያ መስፈርት በጥቅም ላይ ሊውል ለአይችልም።
7. በጨረታ አሸናፊ ሆኖ የሚመረጠው

   ሀ. በጨረታ ግምገማ የቴክኒክ መመዘኛዎችን ማሟላቱ የተረጋገጠ እና አነስተኛ ዋጋ ያቀረበ ተጫራች፣ ወይም

   ለ. ግዥ ፈፃሚ አካል በጨረታው ሰነድ ውስጥ አሸናፊው ተጫራች የሚመረጥበት መስፈርት የገለፀ ከሆነ፣ በጨረታ ሰነዱ የሠፈረውን የጨረታውን ኢኮኖሚያዊ እሴት የሚወስነውን መስፈርት መሠረት በማድረግ በሚካሄድ

ግምገማ ዝቅተኛ ወጋ ያቀረበው ተጫራች አሸናፊ ይሆናል። ሆኖም መስፈርቱ በተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ በአታዝ ሊገለፅ የሚችል ሆኖ በግምገማው ሂደት አንፃራዊ ክብደት የሚሰጠው እና እስከተቻለ ድረስ በገንዘብ የሚገለፅ መሆን አለበት።

8. ግዥ ፈፃሚ አካለ የጨረታ ሰነድ ምርመራና የግምገማውን ውጤት በአጭር የሚገልፅ የግምገማ ሪፖርት ማዘጋጀት አለበት።

አንቀጽ 34 በሚስጥር ስለሚያዙ አሠራሮች፣

1. ጨረታው ከተከፈተበት ጊዜ አንስቶ ከጨረታ መርመራ፣ ከማብራሪያ፣ ከግምገማ እና አሸናፊውን ተጫራች በሚመለከት ከቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ጋር የተያያዙ መረጃዎች በሚስጥርነት መጠበቅ ያለባቸው ሲሆን፣ አሸናፊው ተጫራች እስከሚገለፅ ድረስ ለተጫራቾች ወይም ከሥራው ሂደት ጋር ግንኙነት ለሌላቸው ሰዎች መግለፅ የለባዠውም።
2. ጨረታው ከተከፈተበት ጊዜ አንስቶ ውሉ እስከሚፈረም ድረስ ማናኛውም ተጫራች በማናቸውም አኳኋን የጨረታውን ምርመራና ግምገማ ለማዛባት መሞከር የለበትም።
3. ጨረታው ከጣበት ጊዜ ጀምሮ ውሉ እስከሚፈረም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ እጩ ተወዳዳሪው ከጨረታው ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ከግዥ ፈፃሚው አካል ጋር ግንኙነት ማድረግ የሚችለው በፅሁፍ ብቻ ይሆናል።

አንቀጽ 35 ተጫራቾች ያቀረቡት የመወዳደሪያ ሃሳብ የማይሻሻልበት ሁኔታ፣

ማናቸውም ተጫራች በጨረታው ሰነድ ከተመለከተው ውጪ፣ በጨረታው አሸናፊ ለመሆን ያቀረበውን የመጫረቻ ዋጋ አንዲለውጥ ወይም በሌላ አኳኋን የቀረበውን የመወዳደሪያ ሃሳብ እንዲያሻሽል ወይም ይህንን ለመፈፀም ግዴታ አንዲገባ በቅደመ ሁኔታነት ሊጠየቅ ወይም ሊገደድ አይችልም።

አንቀጽ 36 አሸናፊነትን ስለመግለፅና ውል ስለመፈራረም

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት የመወዳደሪያ ሃሳብ ፀንቶ የሚቆይበት ቀን ከማለፉ በፊት በጨረታው አሸናፊ ለሆነው ተጫራች አሸናፊነቱን መግለፅ አለባቸው። የአሸናፊነት መግለጫ ማስታወቂያ ውሉ የሚፈረምበትን ጊዜ የሚገልፅ ይሆናል። በጨረታው ተሸናፊ ለሆኑ ተጫራቾችም የአሸናፊውን ስም እና የተሸነፉበትን ምክንያት የሚገልፅ ማስታወቂያ ሊደርሳቸው ይገባል።
2. በግዥ ፈፃሚ አካለ እና በአቅራቢው መካከል ውል ተመስርቷል የሚባለው በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች ስምምነት የተደረሰባቸውን ጉዳዮች በሙሉ የሚይዘው የውል ሰነድ ሲፈረም ይሆናል።
3. ግዥ ፈፃሚው አካል ለተሸናፊዎቹ ተጫራቾች ተሸናፊነታቸውን የሚገልፀው ማስታወቂያ ከመድረሱ እና በአንቀጽ 47 የተመለከተው የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት የግዥውን ውል መፈረም የለበትም።

አንቀጽ 37 የውል ማስከበሪያ

አቅራቢው በውሉ መሠረት ባለመፈፀሙ በግዥ ፈፃሚ አካል ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ማካካሻ የሚውል የውል ማስከበሪያ ለግዥ ፈፃሚው አካል መስጠት አለበት። የውል ማስከበሪያ የሚጠየቅባቸው የግዥ ዓይነቶች፣ የውል ማስከበሪያው ዓይነትና መጠን ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

ምዕራፍ ስድስት

ሌሎች የግዥ ዘዴዎች አፈፃፀም ሂደት

አንቀጽ 38 ውስን ጨረታ

የውስን ጨረታ ስርዓቶች ከግልፅ ጨረታ ጋር ተመሳሳይ ሲሆኑ፣ የውስን ጨረታ የሚከተሉትን ልዩ አሠራሮች ይከተላል።

1. የጨረታ ጥሪው በጨረታው ለመሳተፍ ፍላጐት ላላቸው የተወሰኑ እጩ ተወዳዳሪዎች ብቻ ይሳካል። ተጫራቾች አድልዎ በሌለበት ሁኔታ መመረጥ ያለባቸው ሲሆን፣ የሚቻል እስከሆነ ድረስ ጥሪ የሚደረግላቸው እጩ ተወዳዳሪዎች ብዛት ውጤታማ የሆነ ውድድር እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችል መሆን አለበት።
2. ግዥ ፈፃሚ አካላት በውስን ጨረታ ተሳታፊ እንዲሆኑ ጥሪ የሚደረግላቸውን እጩ ተወዳዳሪዎች የሚመርጡት በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ከተመዘገቡት መካከል ይሆናል። አመራረጡ በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ለተመዘገቡ እጩ ተወዳዳሪዎች ፍትሀዊ የሆነ እድል የሚያስገኝ መሆን ይኖርበታል። ከዚህ በላይ የተነገረው ቢኖርም እጩ ተወዳዳሪዎች ጥሪ ቢደረግላቸውም በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ መሆኑን መግለፅ እንዲችሉ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 25/1/ በተደነገገው መሠረት ማስታወቂያ ለማውጣት ይችላል፣
3. ለጨረታው ሰነድ ዝግጅት የሚፈቀደው ጊዜ በግዥ መመሪያ ከተወሰነው አነስተኛ የቀን ብዛት ያነሰ ሲሆን አይችልም።
4. ግዥ ፈፃሚው አካለ የግዥውን ሁኔታ መሠረት በማድረግ የጨረታ ማስከበሪያ ማቅረብ የሚያስፈልግ መሆን ያለመሆኑን ይወስናል።

አንቀጽ 39 ከአንድ አቅራቢ የሚፈፀም ግዥ

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት በአንቀጽ 21/1/ በተደነገገው መሠረት ከአንድ አቅራቢ ግዥ ለመፈፀም ሲፈልጉ ግዥውን መፈፀም ያስፈለገበትን ምክንያት እና የሚገዛውን እቃ ወይም አገልግሎት ጥራት፣ ብዛት የማቅረቢያ ጊዜና ሁኔታዎች የሚያብራራ መግለጫ ማዘጋጀትና ከአቅራቢው ጋር በግልጽ መደራደር አለባቸው። ድርድሩ ከተካሄደ በኋላ በአንቀጽ 21/1/ መሠረት ግዥ ለመፈፀም የሚደረሰው ስምምነት በሁለት ተዋዋይ ወገኖች በሚፈረም ውል መረጋገጥ አለበት።

አንቀጽ 40 በመወዳደሪያ ሃሳብ መጠየቂያ የሚፈፀም ግዥ

1. የመወዳደሪያ ሃሳብ መጠየቂያ ከሶስት ላላነሱ እና ከሰባት ላልበለጡ በግዥ ፈፃሚ አካለ ለሚመጡ እጩ ተወዳዳሪዎች መላክ ይኖርበታል። የምክር አገልግሎቱ የሚጠይቀው ወጪ በመመሪያ ከሚወሰነው የገንዘብ መጠን በላይ ከሆነ እጩ ተወዳዳሪዎች የሚመረጡት በውድድሩ ተሳታፊ ለመሆን የሚፈልጉ ሃሳባቸውን እንዲገልፁ ከተጠየቀ በኋላ ይሆናል።
2. የመወዳደሪያ ሃሳብ መጠየቂያ ቢያንስ የሚከተሉትን መረጀዎች መያዝ አለበት።

   ሀ. የግዥ ፈፃሚውን አካል ስምና አደራሻ፣

   ለ. የሚፈለገውን አገልግሎት የሚያሳይ የማጣቀሻ ፅሁፍ፣

ሐ. የጥቅም ግጭትን ሊያስከትል የሚችል የምክር አገልግሎት በሚሆንበት ጊዜ በዚህ ዓይነቱ ውድድር የሚቀርቡ እጩ ተወዳዳሪዎች ከምክር አገልግሎቱ በማስከተል ከመክር አገልግሎቱ ጋር በተያያዘ ከሚከናወኑ የአቃ አቅርቦትና የግንባታ ሥራዎች ራሳቸውን ማግለል የሚገባቸው መሆኑን የሚገለፅ ማሳሰቢያ፣

መ. የመወዳደሪያ ሃሳቦችን መገምገሚያ መስፈርቶችን፣ ለዋጋና ሌሎች መስፈርቶች የሚሰጠውን ነጥብ፣ መስፈርቶቹ የመወዳደሪያ ሃሳብ በሚገመገምበት ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉበትን አኳኋን፣

ሠ. የመወዳደሪያ ሃሳብ የሚቀርብበትን ቦታና የመጨረሻ ቀን፣

3. እጩ ተወዳዳሪዎች የመወዳደሪያ ሃሳብ ለማዘጋጀት የሚያስችላቸው በቂ ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል።
4. ግዥ ፈፃሚው አካል አንደኛ ሆኖ ከተመረጠው እጩ ተወዳዳሪ ጋር በመወዳደሪያ ሃሳቡ ውስጥ የተመለከተውን የአገልግሎቱን ባህሪ፣ መጠን እና አደረጃጀት የሚመለከት ድርድር ማካሄድ ወይም ማሻሻያ እንዲደረግ መፍቀድ ይችላል።
5. ግዥውን የሚፈፅመው መ/ቤት በአሸናፊነት ሊመርጥ የሚችለው በመወዳደሪያ ሃሳብ መጠየቂያ ሰነድ በተወሰከተው የመገምገሚያ መስፈርት እና ስርዓት መሠረት በሚካሄደው ግምገማ ያቀረበው የመወዳደሪያ ሃሳብ ይበልጥ ጠቃሚ ሆኖ የተገኘውን ተወዳዳሪ ነው።

አንቀጽ 41 በዋጋ ማቅረቢያ የሚካሄድ ግዥ ስርዓት

1. ግዥ ፈፃሚ አካላት የዋጋ ማቅረቢያን ብዛት ካላቸው እጩ ተወዳዳሪዎች መጠየቅ አለባቸው። ስለሆነም የሚቻል እስከሆነ ድርሰ ቢያንስ ሶሶት አቅራቢዎች የዋጋ ማቅረቢያ እንዲሰጡ ሊጠየቁ ይገባል።
2. በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈፀም ግዥ ለእጩ ተወዳዳሪዎች የሚላከው መጠየቂያ የሚቀርበውን እቃ ወይም አገልግሎት ጥራት፣ ብዛት፣ የማቅረቢያ የውል ቃሎች እና ጊዜ እንዲሁም ሌሎች የግዥ ፈፃሚውን አካል ፍላጐቶች የሚይዝ መሆን አለበት።
3. እጩ ተወዳዳሪዎች የዋጋ ማቅረቢያውን ለማዘጋጀት የሚያስችል በቂ ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል።
4. ግዥ ፈፃሚው አካለ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተዘረዘሩትን ተፈላጊ ሁኔታዎች ለሚያሟላ እና አነስተኛ ዋጋ ላቀረበ ተወዳዳሪ የግዥ ትዕዛዝ ይሰጣል።
5. ግዥ ፈፃሚ አካላት በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡ አቅራቢዎች እኩል እድል ማግኘታቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው።

አንቀጽ 42 የሁለት ደረጃ ጨረታ፣

1. ጨረታው የሚከናወነው በሁለት ደረጃ የጨረታ ዘዴ ሲሆን፣ በጨረታው ሰነድ ተጫራቾች በመጀመሪያው ደረጃ ዋጋን ያልጨመረ የመወዳደሪያ ሃሳብ እንዲያቀርቡ ጥሪ ይደረጋል።በጨረታው ሰነድ አቅራቢዎች ከቴክኒክ ጋር ግንኙነት ያላቸውን መግለጫዎች፣ ጥራት ወይም የእቃውን ወይም የአገልግሎቱን ሌሎች ባህሪያት እነዲሁም የአቅርቦቱን ውል ቃሎችና ሁኔታዎች እና አግባብነት እስካለው ድረስ የአቅራቢዎችን የሙያ እና የቴክኒክ ችሎታ እንዲገልፁ ሊጠየቅ ይችላል።

2. በሁለት ደረጃ ጨረታ ዘዴ ሁለተኛ ደረጃ፣ ጨረታውን ያወጣው ግዥ ፈፃሚ አካል ጨረታቸው ውድቅ ያልተደረገው ተጫራቾች አንድ የተለየ ዝርዝርን በሚመለከት ዋጋ እንዲያቀርቡ ይጋብዛል። ይህንን የተለየ ዝርዝር ሲያዘጋጅ መ/ቤቱ በመጀመሪያው የጨረታ ሰነድ ውስጥ ከተቀመጡት ማናቸውም የእቃው ወይም የአገልግሎት የቴክኒክ ወይም የጥራት ባህሪያት እና ሰነዶቹን ለመገምገም እና ለማወዳደር እነዲሁም አሸናፊውን ለመምረጥ ከተቀመጡት መስፈርቶች ውስጥ ማናቸውንም ለመሠረዝ ወይም ለማሻሻል ወይም ከዚህ አዋጅ ጋር የሚስማው አዳዲስ ባህርያትንና መስፈርቶችን ለመጨመር ይችላል። እንደዚህ ያሉት ማናቸውም ሥረዛዎች፣ ማሻሻያዎች ወይም ጭማሪዎች የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሃሳብ እንዲቀርብ በሚተላለፍ ጥሪ ለተጫራቾች መገለጽ አለባቸው። የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሃሳብ ለማቅረብ ያልፈለገ ማናቸውም አቅራቢ የጨረታ ማስከበሪያው ውርስ ላይደረግበት ከጨረታው ውድድር እራሱን ሊያገል ይችላል።
3. በሁለት ደረጃ ጨረታ አሸናፊውን ተጫራች ለመወሰን ግምገማ እና ውድድር የሚደረገው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 33 በተደነገገው መሠረት ይሆናል።
4. ጨረታውን ያወጣው ግዥ ፈፃሚ አካል በጨረታው ግምገማ ከፍተኛ ውጤት ካገኘው አቅራቢ ጋር ከዋጋ በስተቀር በሌሎች ጉዳዮች ላይ ድርድር ሊያደርግ ይችላል።

ምዕራፍ ሰባት

ዓለም ዓቀፍ የግዥ ዘዴ

አንቀጽ 43 ዓለም ዓቀፍ የግዥ ጨረታ

1. ዓለም ዓቀፍ ግልፅ የጨረታ ዘዴ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው የውጭ ኩባንያዎች በጨረታው ተሳታፊ እንዲሆኑ ካልተደረገ በግልፅ ጨረታው ውጤታማ የሆነ ውድድር ሊኖር እንደማይችል የታመነበት እና ግዥው ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ከተመለከተው የገንዘብ መጠን በላይ ሲሆን ነው።
2. ዓለም ዓቀፍ ግልፅ ጨረታ በምዕራፍ 5 የተጠቀሱትን እነዲሁም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ስርዓቶች መከተል አለበት።

   ሀ. የጨረታ ማስታወቂያ እና የጨረታ ሰነዶች የዓለም ዓቀፍ ንግድ መገልገያ በሆነ ቋንቋ መዘጋጀት አለባቸው።

   ለ. የጨረታ ማስታወቂያው በተዘጋጀበት ቋንቋ በሚታተም፣ በቂ ሥርጭት ባለው እና ዓለም ዓቀፍ ውድድርን በሚጋብዝ ጋዜጣ ላይ የጨረታ ማስታወቂያ መታተም አለበት።

   ሐ. የጨረታ ሰነድ የማቅረቢያ ጊዜው የጨረታው ማስታወቂያ ለእጩ ተወዳዳሪዎች እንዲደርስ ለማድረግ እና እጩ ተወዳዳሪዎች የጨረታ መወዳደሪያ ሃሳባቸውን አዘጋጅተው ለማቅረብ የሚያስፈልጋቸውን በቂ ጊዜ የሚፈቅድ መሆን አለበት።

   መ. የእቃና የአገልግሎት ዝርዝር ከአገር ውስጥ ደረጃዎች ጋር የሚጣጣም ሆኖ በዓለም ዓቀፍ ደረጃዎች ወይም በዓለም ዓቀፍ ንግድ በስፋት የሚሠራበትን ደረጃ መሠረት ያደረገ መሆን አለበት።

ሠ. እጩ ተወዳዳሪዎች የመጫረቻ ዋጋቸውን እንዲሁም የሚያቀርቡትን ማናቸውንም የዋስትና ሰነድ በኢትዮጵያ ብር ወይም በጨረታ ሰነዱ በተወሰነተው እና በዓለም ዓቀፍ ንግድ በስፋት በሚሠራበት የገንዘብ ዓይነት እንዲያቀርቡ መፈቀድ አለበት።

ረ. አጠቃላይ እና ልዩ የውል ቃሎችና ሁኔታዎች በዓለም ዓቀፍ ንግድ የሚሠራባቸው መሆን ይኖርባቸዋል።

አንቀጽ 44 ሌሎች ዓለም ዓቀፍ ሥርዓቶች

ከግልጽ ጨረታ ውጪ እንደውስን ጨረታ ወይም የመወዳደሪያ ሃሳብ መጠየቂያ ባሉት የግዥ ዘዴዎች፣ የውጭ አገር ኩባንያዎች እንዲሳተፉ ካለተደረገ ውጤታማ የሆነ ውድድር ሊኖር እንደማይችል ከታመነበት ከምዕራፍ አምስት በተጨማሪ እስከተቻለ ድረስ የአንቀጽ 40/2/ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል።

ምዕራፍ ስምንት

በመንግስት ግዥ ላይ ስለሚቀርብ አቤቱታ

አንቀጽ 45 ጠቅላላ

1. የዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ግዥውን በፈፀመው አካል የተከናወነው ወይም ሳይከናወን የቀረው ተግባር የዚህን አዋጅ፣ የግዥ መመሪያውን ወይም እነዚህን መሠረት በማድረግ የተላለፉ ትዕዛዞችን ይጥላል ብሎ የሚያምን እጩ ተወዳዳሪ በአስተዳደር አካላት ተጣርቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል።
2. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሠረት አቤቱታ ሊቀርብባቸው አይችልም።
   ሀ. በምዕራፍ አራት በተደነገገው መሠረት የሚከናወን የግዥ ዘዴዎች ምርጫ፣
   ለ. በአንቀጽ 17 መሠረት ጨረታን፣ የመወዳደሪያ ሃሳብን ወይም የዋጋ ማቅረቢያን ውድቅ ለማድረግ የሚሰጥ ውሳኔ፣
3. ግዥ ፈፃሚው አካል በጨረታው አሸናፊ ከሆነው ተወዳዳሪ ጋር የግዥ ውል ከፈረመ በኋላ፣ ውድድሩ ከዚህ ደረጃ እስከሚደርስ ድረስ በተከናወኑ ወይም ሳይከናወኑ በቀሩ ተግባራት ምክንያት የሚቀርቡ አቤቱታዎች በአስተዳደር አካላት ሊታዩ አይችሉም።

አንቀጽ 46 ለግዥ ፈፃሚው አካል የበላይ ኃላፊ ስለሚቀርቡ አቤቱታዎች

1. በግዥ ፈፃሚው አካል በተከናወነ ወይም ሳይከናወን በቀረ ተግባር ምክንያት የሚቀርብ አቤቱታ በመጀመሪያ ደረጃ መቅረብ ያለበት ለግዥ ፈፃሚው አካል የበላይ ኃላፊ ይሆናል።
2. እጩ ተወዳዳሪው አቤቱታውን ሊያቀርብ የሚችለው ለአቤቱታው መሠረት የሆነውን ውሳኔ ካወቀበት ወይም ማወቅ ይገባው ከነበረበት ቀን ጀምበሮ በአመስት የሥራ ቀን ጊዜ ውስጥ ይሆናል።
3. አቤቱታው በሁለቱ ወገኖች መካከል በሚደረግ ስምምነት ካልተፈታ በስተቀር የግዥ ፈፃሚው አካል የበላይ ኃላፊ የግዥውን አፈፃፀም ማገድ እና አቤቱታው ከቀረበበት ቀን አንስቶ በ 15 ቀን ጊዜ ውስጥ፣ ውሳኔው የተሰጠበትን መክንያት ወይም አቤቱታው ተቀባይነት ያገኘ ከሆነ የሚወሰደውን የማስተካከያ እርምጃ በመጥቀስ የፅሁፍ ውሳኔ መስጠት አለበት።

4. የግዥ ፈፃሚው አካል የበላይ ኃላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ ወይም ተወዳዳሪው በግዥ ፈፃሚው አካል የበላይ ኃላፊ ውሳኔ ያልረካ እንደሆነ የግዥ ፈፃሚው አካል ውሳኔ ከተገለፀለት ቀን አንስቶ በሚቆጠር 5 የሥራ ቀን ጊዜ ውስጥ ለቢሮው አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል።

አንቀጽ 47 ለቢሮው ስለሚቀርብ አቤቱታ

1. ቢሮው አቤቱታ ሲቀርብለት ወዲያውኑ አግባብ ላለው ግዥ ፈፃሚ አካል አቤቱታ የቀረበ መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ ይልካለ። አቤቱታ የቀረበ መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ እንደተሳካ ግዥ ፈፃሚው አካል ቢሮው በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ማናቸውንም ቀጣይ እንቅስቃሴ ወዲያውማቆም አለበት።
2. ቢሮው የእጩ ተወዳዳሪውን አቤቱታ ውድቅ ካላደረገው በስተቀር፣ ግዥ ፈፃሚው አካል ሕጉን ያልጠበቀ ተግባር እንዳያከናውን እና ውሳኔ እንዳይሰጥ ሊያግድ ወይም ከሕግ ውጪ የሆነውን የዓዥ ሥርዓት እንዳይከተል ሊያደርገ ወይም ግዥ ፈፃሚው አካል በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ሥራውን እንዲያከናውን ትዕዛዝ ሊያስተላልፍ፣ አሸናፊውን ተጫራች ከመምረጥ ወይም ውል ከመፈረም ጋር ከተያያዙ ውሳኔዎች በስተቀር ግዥ ፈፃሚው አካል ሥራውን እንዲያከናውን ወይም ግዥ ፈፃሚው አካል ከሕግ ውጪ ያከናወነው ተግባር ወይም የሰጠው ውሳኔ በሙሉ ወይም በከፊል ቀሪ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል።
3. ቢሮው በአቤቱታ ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ስለአቤቱታው ለማወቅ ፍላጐት ላላቸው እጩ ተወዳዳሪዎች ማሳወቅ፣ ከእነዚህ ተወዳዳሪዎች እና ከግዥ ፈፃሚው አካል የቀረበውን መረጃና መከራከሪያ መመርመር አለበት።
4. ቢሮው አቤቱታው ከቀረበለት ቀን አንስቶ በ 15 ቀናት ውስጥ ለውሳኔው መሠረት የሆኑትን ምክንያቶች እና የተወሰዱትን የመፍትሄ እርምጃዎች በመጥቀስ ውሳኔ መስጠት አለበት።

ምዕራፍ ዘጠኝ

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 48 ጥፋቶችና ቅጣቶች

1. ይህንን አዋጅ ለመፈፀም በማናቸውም የመንግስት መ/ቤት የተሾመ ወይም የተመደበ ሰው፣
   ሀ. በሕግ መሠረት ሊከፈለው ከሚገባ በስተቀር የተመደበበትን ሥራ በማከናወን ማናቸውንም ክፍያ ከተቀበለ፣
   ለ. የመንግስት መ/ቤትን የግዥ አሠራር በማጭበርበር ወይም ሌላ ሰው እንዲያጭበረብር ሁኔታዎችን በማመቻቸት የተባበረ ወይም ያሴረ፣
   ሐ. ሕጉን የጣሰ ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው ሕጉ እንዲጣስ ሆን ብሎ የፈቀደ፣
   መ. በፈቃደኝነት በማናቸውም መንገድ ሀሰተኛ ሰነድ ላይ የፈረመ ወይም የመዘገበ ወይም ሀሰተኛ የምስክር ወረቀት የሰጠ፣ ከብር 25000 /ከሃያ አምስት ሺህ ብር/ በማያንስና ከብር 35000 /ከሰላሳ አምስት ሺህ ብር/ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫና ከ 10 ዓመት በማያንስና ከ 14 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስሥራት ይቀጣል።
2. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለማስፈፀም የተቀጠረ ማናቸውም የግዥ ባለሙያ በዚህ አዋጅ ይፋ እንዲሆን ከታዘዘው ዓይነት መረጃ በስተቀር፣

ሀ. ግዥውን በማስፈፀም ረገድ ባለው ስልጣን ወይም ኃላፊነት ምክንያት ያወቀውን የሌላ ሰው ማናቸውንም መረጃ ለማናቸውም ሌላ ሰው ወይም የዚህ ሰው ወኪል ለሆነ ሰው አሳልፎ የሰጠ፣

ለ. በዚህ አዋጅ መሠረት ግዥን በማከናወን ረገድ ያለውን ስልጣን ለማስፈፀም ወይም የስራ ግዴታውን ለመወጣት እንዲያስችል ግዥውን በሚፈጽመው መ/ቤት ዘንድ የሚገኘውን ማናቸውንም መረጃ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ካልሆነ በስተቀር ለሶስተኛ ወገን አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፣ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 10000 /አስር ሺህ ብር/ በማያንስ የገንዘብ መቀጫ እና ከ 2 /ሁለት/ ዓመት በማያንስ፣ ከ 5 /ከአምስት/ ዓመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል።

3. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ሥራ ላይ ለማዋል ግዥውን በሚፈፅመው መ/ቤት የተቀጠረ ሠራተኛ፣

ሀ. በቀጥታ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የገንዘብ ወይም ሌላ አይነት ክፍያ ወይም ስጦታ እንዲደረግለት የጠየቀ ወይም የተቀበለ ለክፍያው ወይም ለስጦታው ተስፋ ወይም መያዣ የጠየቀ ወይም የተቀበለ፣ ወይም

ለ. በግዥ ተግባር ላይ ማጭበርበር ወይም ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር ወይም ከተሰጠው ኃላፊነት መልካም አፈጎነም ጋር የሚቃረን ተግባር ለመፈፀም፣ ማድረግ የሚገባውን ከማድረግ ለመታቀብ፣ ተገቢ ያልሆነን ነገር ለመፍቀድ፣ በግዥ ላይ የሚፈፀምን የማጭበርበር ተግባር ለመደበቅ፣ ወይም በሚሰጥር ለመተግበር ውል የገባ ወይም በሚገባው ውል ውስጥ በዚህ ተግባር መተባበሩን የሚያሳይ ስምምነት የሰጠ፣ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 50000 /ሃምሳ ሺህ ብር/ የማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና 10 /አስር/ ዓመት በማያንስ ከ 20 /ከሃያ/ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል።

4. ማንኛውም ሰው በመንግስት ግዥ ላይ ለተሾመ ወይም ለተመደበ ሰው፣

ሀ. የቀረበለትን ውሳኔ በመጠበቅ ላይ ያለውን ጉዳይ ወይም በሥራ ኃላፊነቱ ምክንያት ሊቀረብለት በሚችል ጉዳይ ላይ የሚሰጠውን ውሳኔ ወይም የሚወሰደውን እርምጃ ለማዛባት ወይም፣

ለ. በመንግስት ግዥ ላይ የማጭበርበር ድርጊት እንዲፈፀም ወይም ድርጊቱ ሲፈፀም እንዲረዳ ወይም እንዲተባበር ወይም ለድርጊቱ መፈፀም ሁኔታዎችን ለማመቻቸት እንዲስማማ፣ እንዲመሳጠር ወይም እንዲፈቀድ ለማድረግ በማሰብ ጉዞ ለመስጠት ቃል ከገባለት፣ ካቀረበለት ወይም ከሰጠው ጥፋተኛ ሆኖ መገኘቱ በፈርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብረ 50000 /ሃምሳ ሺህ ብር/ ያላነሰ የገንዘብ መቀጫ እና ከ 10 /ከአስር/ ዓመት የማያንስ እና ከ 20 /ከሃያ/ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል።

አንቀጽ 49 ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

1. ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የአፋር ክልል መስተዳድር ምክር ቤት እንደአስፈላጊነቱ ደንብ ሊያወጣ ይችላል።
2. ይህን አዋጅ ለማስፈፀም ቢሮው መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

አንቀጽ 50 ውሎች የሚመሩባቸው ሕጐች፣

የዚህ አዋጅ ልዩ ድንጋጌዎች አንደተጠበቁ ሆነው የመንግስት ግዥ አፈፃፀም በፍትሃ ብሄር ሕግ የአስተዳደር ክፍል መስሪያ ቤቶች ስለሚያደርጓቸው ውሎች በተደነገገው መሠረት የሚመራ ይሆናል።

አንቀጽ 51 የተሻሩና ተፈፃሚ የማይሆኑ ሕጐች

1. የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 7/1990 ዓ.ም አንቀጽ 53-56 ተሽረዋል።
2. የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፋይናንስ ደንብ ቁጥር 2/1991 ዓ.ም አንቀጽ 65-72፣ ተሽረዋል።
3. ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

አንቀጽ **52** አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሠመራ

ሰኔ **2000** ዓ.ም

እስማኤል አሊ ሲሮ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ርዕሰ መስተዳድር